# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE NINEጭንቅ ፣ ድንብ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ወ/ሮ ሉሊት MOVES INTO THE NEW HOME**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: ትዕግስት TALKS TO ንጉሴ DURING SCHOOL BREAK**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 3: አቶ ሙላቱ QUITS HIS JOB AS አቶ ጃለታ WATCHMAN**

- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- የተወሰኑ ሰካራሞች
-

## SCENE 4: ምህረት AND ወ/ሮ ሉሊት HAVE A MOTHER-DAUGHTER CHAT

- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- ምህረት (F, 15)

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ትምህርታዊ ድራማ ክፍል ዘጠኝ ነዉ። በዚህ ተከታታይ ጭዉዉት፤ እጅግ በጣም ጥሩ እና የተለየ ተብሎ በሚታወቀው ቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩትን ንጉሴ፣ ዳንኤል እና ምህረት የተባሉ ሶስት ተማሪዎችን እንከታተላለን፡፡ እስከ አሁን የሆነውን መለስ ብለን ስናታውስ፤
ባለፈው ጊዜ ምህረት በከባድ የሆድ ቁርጠት በመሰቃየት ላይ ነበረች፡፡ የሆድ ቁርጠቱ የተለመደ አይነት አልነበረም…ከዝያም ምህረት መጸዳጃ ቤት ሳለች፣ ያልጠበቀችውን ነገር አይታለች፡፡

2. ምህረት (EP 08, 75): "" ትዕግስት ትዕግስት! እረ እየደማሁ ነኝ!"!"
3. ትዕግስት: " አየሽ፣ ፔሬድሽ ማለት የወር አበባሽ ነው ማለት ነዉ፡፡ምህረት እንኳን ደስ አለሽ!አሁን ሴት ሆንሻል! (chuckles)

በእዚህ አስጨናቂ ሁኔታ ምህረትን የረዳቻት የልብ ጓደኛዋ ትዕግስት ናት፡፡ ሆኖም ትዕግስት መንታ ገፅታ ነው ያላት፡፡ ምህረት የማታውቀው ነገር ቢኖር አድናቂዋ ዳንኤልን ትዕግስት ከበስተጀርባዋ ሆና ለማግለል መፈለጓን ነው

4. **ትዕግስት (EP 06, 99):** "ዳንኤል፣ አብረን ልንደሰት ልንግባባ እንደምንችል ይሰማኛል!"

5. **DAN:** " መልካም...ህምምም...ይቅርታ፣ ትዕግስት፣ ድንገት በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል፤ አሁን ግን መሄድ አለብኝ። ምህረትን ሳላገኛት ካገኘሻት ሰላም በይልኝ።"

6. **SFX: STEPS DAN LEAVES**

7. **ትዕግስት (LINE 103): (thinking to herself)** "እሺ. ዳንኤል፤ ለማግኘት ብዙ መታገልን ትፈልጋለህ? ትዕግስት ማን እንደሆነች አሳይሀለሁ። ይህ ገና ጅማሬዬ ነው!"

ምህረት እቤት ውስጥ እንኳ ምን እየተካሄደ እንደሆነ በውል አልተገነዘበችም። አባቷ ቤተሰቡን ከድህነት ለማውጣት አቀድኩ በሚል-አዲስ የተወለደችው እህቷን ለአካባቢው ሀብታም ነጋዴ ሸጠዋታል። በቀጣይ ምን ይከሰት ይሆን? የሚሆነውን ዛሬ በምናደምጠዉ "ጨንቆኛል፣ ጠቦኛል" በተሰኘዉ የጭዉዉቱ ዘጠነኛ ክፍል እንከታተል። የምህረት እናት፣ ወ/ሮ ሉሊት ፣ ከሐኪም ቤት መልቀቅያ አግኝተው ወጥተዋል። ባለቤታቸው፣ አቶ ሙላቱ ደግሞ፣ ወ/ሮ ሉሊትን ከሐኪም ቤት ወደ አዲሱ ቤት አድርሰዋቸዋልል። ይሁንና ወ/ሮ ሉሊት ራሳቸውን ጨርሶ በማያውቋቸው ጎረቤቶች መሀል በማግኘታቸው ግራ የተጋቡ ይመስላል...

## SCENE 1: ወ/ሮ ሉሊት MOVES INTO THE NEW HOME

8. **SFX: PADLOCKED DOOR BEING OPENED WITH KEY**

9. **SFX: DOOR OPENING**

10. **አቶ ሙላቱ፡ (proud) ወ/ሮ ሉሊት ፣ወደ አዲሱ ቤትሽ እንኳን ደህና መጣሽ። እንደምትወጂው ተስፋ አለኝ።**

11. **ወ/ሮ ሉሊት : (amazed) ይህ አዲሱ ቤታችን ነው? ኧረግ ኧረግ! ሙላቱ፣ በጣም ቆንጆ ነው**

12. **SFX: FOOTSTEPS: TWO PEOPLE ENTERING**

13. **SFX: DOOR CLOSING**

14. **አቶ ሙላቱ፡ ተመልከቺ! አዳዲስ የቤት እቃዎች ገዝቼአለሁ። አሁን እዚህ ኤሌክትሪክ ስላለን ብዪ ትንሽ ቴቪ.ምገዝቻለሁ። እና ከሁሉም በላይ ግን ዋናዉ …**

15. **SFX: TAP BEING TURNED ON - WATER STARTS FLOWING**

16. **ወ/ሮ ሉሊት : ጭራሽ የውሃ ቧንቧ ቀጥታ ቤቴ ውስጥ! ሁሉም ነገር ህልም ይመስላል። ከእዚህ በኋላ ውሃ አንገዛም እያልከኝ ነው?**

17. **አቶ ሙላቱ፡ በእርግጥ መክፈል አለብን። ግን አንቺ እና ምህረት ሌሊት ተነስታችሁ ለውሃ ሰልፍ በመሰለፍ ሰዓታት አታባክኑም። አየሽ፣ ሉሊት -የድህነትን እና የተስፋ መቁረጥ ኑሮን ደህና ሰንብት ብለነዋል።**

18. **ወ/ሮ ሉሊት ፡ግን አቶ ሙላቱ፣ ይህን ሁሉ ገንዘብ ከየት -- (stops, realizes) አመጣኸው…ይህ መቼም አይሆንም! አላደረከውም! ልጃችንን ለዚህ ሸጫታለሁ አትበለኝ! ለአንዱ እሰጣታለሁ ብለኸኝ ነበር! (starts screaming) ንገረኝ፣ እውነቱን ንገረኝ!!**

**19. አቶ ሙላቱ:** ሂይ፣ ተረጋጊ! ወ/ሮ ሉሊት ፣ አድምጪኝ፣ ማድረግ ነበረብኝ። ከድህነት መውጫ ሌላ ገንዘብ አልነበረንም። ልጅቷ ካለ እኛ የተሻለ ኑሮ ትኖራለች! ምርጥ ወላጆች አግኝቼላታለሁ! እና አንቺ? ለዘለአለም በዚያ ጎስቋላ መንደርስ ውስጥ ዕድሜሽን መግፋት ትፈልጊያለሽ? ሉሊት፣ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ሌላ ልጅ መውለድ እንችላለን። የምትፈልጊው ይህ ከሆነ አስር ተጨማሪ ልጆች መውለድ እንችላለን።

**20. ወ/ሮ ሉሊት :** እስከ አሁን ሶስት ልጆቼን ወስደህብኛል! ሁለቱ ትንንሽ ወንዶች ልጆቼ እህትህ ጋር ላቦሪያ ውስጥ እንደሚኖሩ ብትነግረኝም አላመንኩህም። እህትህ መጥታ ከወሰደቻቸው ጊዜ አንስቶ አናግሬአቸው እንኳ አላውቅም! **(breaks down in tears)** አሁን ትንሿ ሴት ልጄን ሸጥካት- እና ለምን? ለቤት እቃ እና ቲቪ? የልጃችን ዋጋ ይህ ነው?**KW BEGIN**

**21. አቶ ሙላቱ:** **(furious)** አንቺ ሴት ማነብነብሽን አቁሚልኝ! ሰማሽ? ማድረግ የነበረብኝን አደረኩ። እና ለመጨረሻ ጊዜ የማስጠነቅቅሽ ስለእዚህ ጉዳይ ትንፍሽ አላለሁ ብትዪ ከዚያ በኋላ መራመድም ሆነ መናገር እንደማትችዪ አረጋግጥልሻለሁ።

**22. ወ/ሮ ሉሊት :** **(still angry)** ታውቃለህ ሙላቱ? ከዚህ በኋላ ለእዚህ ለዛቻህ ቅንጣት ታህል ፍራቻ የለኝም። የምትፈልገው እኔን መግደል ከሆነ ይኸው ግደለኝ። የምሳሳለትንን ሁሉን ነገሬን ወስደህብኛል።

**23. አቶ ሙላቱ:** **(furious)** ሉሊት ፣ አትገፋፊኝ። እቺ ምን ሰበብ …

**KW END**

**24. SFX: DOOR BEING OPENED**

**25. SFX: FOOTSTEPS - ምህረት COMES IN**

**26. ምህረት:** (faintly) ሃይ፣ አባዬ፣ እማ እንዴት ነሽ ! ባይገርማችሁ ክርክራችሁ ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ባላይ ይሰማ ነበር፤ ሰምቻችኋለሁ። እማዬ ምንድን ነው? አዲሱ ቤታችንን አልወደድሽውም?

**27. ወ/ሮ ሉሊት :** (surprised) ምህረት እዚህ ምን ታደርጊያለሽ? ትምህርት ቤት መሄድ አልነበረብሽም??

**28. አቶ ሙላቱ:** አዎ፣ ምህረት በዚህ ሰዓት ለምን መጣሽ?

**29. ምህረት:** ታሪኩ ረጅም ነው አባዬ !። እማ ለብቻሽ ላናግርሽ እችላለሁ?

**30. ወ/ሮ ሉሊት :** አዎ የኔ ልጅ! እኔም የሆነ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ። እናትና ልጅ ልብ ለልብ የምንነጋገርበት ጊዜው አሁን ነው።

**31. አቶ ሙላቱ:** ነው እንዴ! በሉዋ ተባብራችሁ ማጅራቴን በሉኝ? ወቸ ጉድ? እንደያ ነው ነገሩ? በገዛ ቤቴ ልትገለብጡኝ !!

**32. SFX: አቶ ሙላቱ'S FOOTSTEPS WALKING RAPIDLY TO THE DOOR**

**33. አቶ ሙላቱ:** ይሄማ ፈጽሞ እንዲከሰት አልፈቅድም!!

**34. SFX: DOOR BANGS**

**35. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: ትዕግስት TALKS TO ንጉሴ DURING SCHOOL BREAK

**36. SFX: SCHOOL BELL RINGS**

**37. SCHOOLYARD ATMO**

**38. ትዕግስት:** ንጉሴ፣ ላናግርህ እችላለሁ?

**39. ንጉሴ:** **(bluntly)** አልችልም፡፡

**40. ትዕግስት:** ስለ ምህረት እኮ ነው.

**41. ንጉሴ:** **(interested)** ስለእሷ ነው እንዴ እ ትዕግስት፣ ምንድን ነው? ስለ ምህረት ምን??

**42. ትዕግስት:** ማለቴ ነገሩን አስተውለኸው እንደሆነ እንጃ ብቻ ግን……

**43. ንጉሴ:** ግን ምን? በያ ተናገሪው ትዕግስት!,,እ እ እ የእረፍት ሰዓት እያለቀ እኮ ነው፡፡.

**44. ትዕግስት:** ጥሩ…ዳንኤል ነው፡፡

**45. ንጉሴ:** ምን አደረገ? **(grinning teeth in anger)** ያ የማይረባ ደደብ ምን አደረገ? ያኔ የተደባደብን ግዜ ጥርሱን ባራግፍለት ጥሩ ነበር፡፡

**46. ትዕግስት:** ዳንኤል ለትዕግስት በጣም ብዙ ገንዘብ ሰጥቷታል፡፡

**47. ንጉሴ:** **(shocked)** ምን አደረገ? ትዕግስት፣ ግን እርግጠኛ ነሽ?

**48. ትዕግስት:** ፖስታውን የከፈትኩት እኮ እኔ ነኝ፡፡ ንጉሴ፤ ገንዘቡን በአይኔ

አይቻለሁ።

**KW BEGIN**

**49. ንጉሴ:** እና ተቀበለች?

**50. ትዕግስት:** **(chuckles)** አስቂኝ ጥያቄ ነው። ከአድናቂዋ ገንዘብ የማትቀበል የትኛዋ ሴት ነች?

**51. ንጉሴ:** ወስዳለች እያልሽኝ ነው?

**52. ትዕግስት:** አዎዎ ወስዳለች! ምን አልባትም እስከ አሁን ጨርሳ አጥፍታዋለች!

**53. ንጉሴ:** አላምንሽም! ምህረት እንደ እዛ አይነት ሴት አይደለችም፣

**54. ትዕግስት:** ይልቁንስ ስማ፣ ከማን ጋር ፍጥጫ ላይ እንሆንክ ላሳዉቅህ ፈልጌ ነው። ማመን አለማመን የራስህ ችግር ነው።

**55. ንጉሴ:** ነው እንዴ። እሺ፣ ስላሳወቅሽኝ አመሰግናለሁ። አንድ ጥያቄ፤- ምህረት ምን ሆና ነበር? ርዕሰ መምህርቷስ ለምንድን ነው ሰዓት ሳይደርስ ወደ ቤቷ እንድትሄድ የለቀቀቻት?

**56. ትዕግስት:** ያንን ልነግርህ ስለማልችል እራሷን ጠይቃት።

**57. ንጉሴ:** **(depressed)** እሺ።

**KW END**

**58. ትዕግስት:** ይኸውልህ፣ የሆነ ሀሳብ መጣልኝ። ከተስማማህ ሁለታችንም የምንፈልገውን እናገኛለን።

**59. ንጉሴ:** እሺ ቀጥዪ።

**60. ትዕግስት:** ምናልባት አንተም ሳትገምት አትቀርም፤ ዳንኤልን ፈልጌዋለሁ። ስለእዚህ እርሱን እንድቀርበው ከረዳኸኝ አንተን ደግሞ ከምህረት ጋር አቀራርብሀለሁ።

**61. ንጉሴ:** **(thinking)** ህምምም። ያዉ እንደምታውቂው ዳንኤል እና እኔ የልብ ጓደኞች አይደለንም… እንዴት ይረዳኛል ብለሽ ታስቢያለሽ?

**62. ትዕግስት:** ቀላል ነው! እንደ ምንም ብለህ ጓደኛ አድርገዋ።

**63. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: አቶ ሙላቱ QUITS HIS JOB AS አቶ ጃለታ WATCHMAN**

**64. LOCAL BAR ATMO**

**65. አቶ ሙላቱ:** **(drunk, in the middle of telling a story)** ከዚያም ወደ ቤት አመጣኋት…እስቲ አስቡት፣ ጓዶቼ፣ ወደ አዲሱ ቆንጆ ቤት – **(stops)**

**66. SFX: MOBILE PHONE RINGING**

**67. አቶ ሙላቱ:** **(picks up, annoyed)** አቤት፣ ሙላቱ ነኝ። ማን ልበል?

**68. አቶ ጃለታ:** **(on the phone)** አቶ ሙላቱ! አለቃህ ጃለታ ነኝ፤ የንጉሴ አባት። ስራ ለምን አልገባህም? ምን አይነት ችግር እየፈጠርክ እንደሆነ አውቀኸዋል? ቤቱን ያለ ዘበኛ ትቼው መሄድ አልችልም። አሁኑኑ መምጣት አለብህ፣ አለበለዚያ ግን …

69. አቶ ሙላቱ፡ ወይም ምን? ምምም?...ምን ጃለታ?

70. አቶ ጃለታ፡ አለበለዚያ አባርርሀለሁ!

71. አቶ ሙላቱ፡ (laughs) አባርርሃለሁ? የምታባርረኝ በረሮ መሰልኩህ?

72. SFX: LAUGHTER FROM DRUNKARDS

73. አቶ ጃለታ፡ (furious) አቶ ሙላቱ፣ ቀልድ አይደለም! ከስራ አስወጥቼህ ሌላ ሰው እተካበታለሁ! አንተ ያለብህበትን ቦታ ስንት ሰው እንደሚመኘው ታውቃለህ?

74. አቶ ሙላቱ፡ ምን ታስፈራራኛለህ! ብትፈልግ አባርረኝ፣ ቀንሰኝ የፈለከውን፡፡ እንዴ! እንዴ ቆይ እንደውም አንድ የተሻለ ሀሳብ አለኝ፡፡ ስማ ይኸውልህ እንደውም አንተ ሳታባርረኝ በፊት እኔ ቀድሜ አባርሬሃለሁ! በቃኝ!

75. SFX: APPLAUSE FROM DRUNKARDS

KW BEGIN

76. አቶ ጃለታ፡ ትልቅ ስህተት እየሰራህ ነው፣ አቶ ሙላቱ፡፡ ወደ ስራዬ መልሰኝ ብለህ በሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመለመን ካልመጣህ ምን አለ በለኝ፣

77. አቶ ሙላቱ፡ (sarcastic) ስማ አቶ ጃለታ፣ አትጨነቅ- ያንተን ንብረት ለመጠበቅ አልመጣም፡፡ አሁን የምጠብቀው የራሴ ንብረት አለኝ፡፡

78. SFX: MORE APPLAUSE FROM DRUNKARDS

**79. አቶ ጃለታ:** የመጨረሻ እድል፣ አቶ ሙላቱ፥ እንዲህ የራራሁልህ ለቤተሰቦችህ ስል ነው።

**80 አቶ ሙላቱ: (angry)** የኔን ቤተሰቦች እዚህ ዉስጥ አታስገባ! ሰማኸኝ!ስለኔ ቤተሰቦች ምንም የምታዉቀዉ ነገር የለም! የራስህን ስራ ብቻ እንድተሰራ አስጠነቅቅሃለሁ ጃለታ!

**KW END**

**81. SFX: MOBILE PHONE DISCONNECTED**

**82. አቶ ሙላቱ:** ያ የቀደሞ አለቃዬ እንዴት ያለ ጂል ቢጤ ነው ባካችሁ፤ ነሆለል። በቃ በእሱ ቤት ገንዘብ ያለው እርሱ ብቻ ነው የሚመስለው! **(To friends)** ወዳጆቼ፣ የሚቀጥለው ዙር የእኔ ነው! ቀኑ እስኪገኛኝ ድረስ እንጠጣ!

**83. SFX: DRUNKARDS APPLAUD AND CHEER WILDLY**

**84. MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 4: ምህረት AND ወ/ሮ ሉሊት HAVE A MOTHER-DAUGHTER CHAT</u>

**85. SFX: ONIONS BEING CHOPPED**

**86. ወ/ሮ ሉሊት :** ምህረት ሽንኩርቱን በመላጥ ስለረዳሽኝ አመሰግናለሁ። ምን እንደገጠመሽ ንገሪኝ እስቲ። በጭራሽ ሌላ ሰው መስለሻል። በጣም አደግሽ፤ ተለወጥሽ።

**87. ምህረት:** ከአንቺ ጋር መነጋገር የፈለኩት ይህንኑ ነበር። አዎ እማ ፤ የመጀመሪያ ፔሬዴን አየሁ።

**KW BEGIN**

**SILENCE**

88. ምህረት: እማዬ እያልኩሽ ያለሁት እኮ የመጀመሪያውን የወር አበባዬን አየሁ ነው።

89. ወ/ሮ ሉሊት : (bluntly) ሰማሁሽ፥ ልጄ ምን ተሰማሽ ታድያ? ሁሉንም ነገር ቻልሽበት?

90. ምህረት: እየቻልኩበት ነው። ግን እማዬ፣ ቀደም ሲል ስለእዚህ ለምን አልነገርሽኝም? ትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት አፍረት በአፍረት እንደሆንኩ ባየሽ።

91. ወ/ሮ ሉሊት : (shocked) ውይ በሞትኩት! ጭራሽ ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኜ ጀመረኝ እንዳትይኝ ብቻ፥

92. ምህረት: አዎ። እዚያ ነው የጀመረኝ። እንደ እድል ሆኖ ግን ትዕግስት ረዳችኝ። ግን ጥያቄዬን አልመለሽም። ለምን ቀደም ብዬለእዚህ እንደዘጋጅ አላደረግሽኝም??

**KW END**

93. ወ/ሮ ሉሊት : ልጄ፣ ይቅርታ። ሁልጊዜም ትንሽ ልጅ እንደሆንሽ ነበር የማስበው። አሁን ግን ማወቅ ያለብሽን ሁሉ ልነግርሽ እችላለሁ።

94. ምህረት: ዘገየሽ እማ ፤ ርዕሰ መምህርቷ ነግረዉኛል።

95. ወ/ሮ ሉሊት ፡ በሞትኩት፣ ነገሩሽ! ለዚህ ነዋ ከተለመደው ጊዜ አሁን ቀድመሽ የመጣሽው?

96. ምህረት፡ አዎ።

97. ወ/ሮ ሉሊት ፡ ምህረቴ እነዚህ ነገሮች የተለመዱ ናቸው። የወር አበባ ስላየሽ ከክፍል መቅረት የለብሽም።

98. ምህረት፡ ምንአልባት ለአንቺ የተለመደ ነው። ለእኔ ግን አይደለም። ለጊዜው ሁሉም ነገር በጣም አስቸጋሪ ነው። አዲስ ትምህርት ቤት፣ ፔሬድ፣ ምናምን። የወንዶቹማ አይነሳ፤

99. SFX: ONION CHOPPING STOPS

100. ወ/ሮ ሉሊት ፡ (interested) ወንዶቹ? የትኞቹ ወንዶች? ምህረት፣ ያልነገርሽኝ የሆነ ነገር አለ?

101. ምህረት፡ ክፍል ውስጥ የፈለጉኝ ሁለት ወንዶች አሉ። አንደኛው የፍቅር ደብዳቤ ላከልኝ። ሌላኛው ደግሞ ገንዘብ ሰጠኝ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፣ እማዬ። ምክርሽን የፈለኩት ለዚህ ነው። በእውነት ግራ ገብቶኛል።

102. ወ/ሮ ሉሊት ፡ (panicking) እንዴ የኔ ልጅ ፣ እንነጋገራለን እንጂ፣ አይዞሽ፡ ግን እስቲ ንገሪኝ፣ ገንዘቡን ተቀበልሽው?

103. ምህረት፡ (humming and hawing) ኧ…አዎ

104. ወ/ሮ ሉሊት ፡ ምን አደረግሽበት?

105. ምህረት: ለሆስፒታል ከፈልኩበት።

106. ወ/ሮ ሉሊት ፡ እህ፣ ለሆስፒታል ከፈልሽዉ? እኔ ደግሞ አባትሽ…ለማንኛውም። የትምህርት ቤት ጓደኛሽ ገንዘቡን ሰጥቶሽ በምላሹ የሆነ ነገር እንድትሰጪው ፈልጓል?

107. ምህረት: (stunned) ምን? አልፈለገም! ምንም አላደረኩም። ግን …

108. ወ/ሮ ሉሊት ፡ ግን ምን? ተናገሪ፣ ምህረት። ንገሪኝ-ግን ምን?

109. ምህረት: ግን ከሁለት አንዳቸው ድንገት ባየኝ ቁጥር…እኔም አየውና…ጭንቅ ድንብር እላለሁ።

110. ወ/ሮ ሉሊት (sighs quietly)

111. MUSIC INTERLUDE

**112. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

እንዲህ የእናት እና የሴት ልጅ የልብ ለልብ ጨዋታ በአፍሪቃውያን ቤት ውስጥ አብዛኛዉ ጊዜ የሚሰማ ባይሆንም፤ ቅሉ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው ። በዚሁ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ-ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ" በሚል የጀመርነዉን ተከታታይ ጭዉዉት ክፍል ዘጠኝ እናጠናቅቃለን፡፡ ነገሩ ሁሉ እየተሟሟቀ ነዉ። በቀጣይ ምን እንደሚከሰት ለማወቅ የሚቀጥለዉን ድራማ ያድምጡ። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። ድራማዉን ከድረገጻችን ወደ ግል መዝገቦ ላይም ማውረድ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ዳግም እስክንገናኝ ለዛሬው በእዚሁ እንሰናበት፤ ጤና ይስጥልን!